## ግንቦት ሰባት v. ግንቦት ሃያ: ግንቦት ሰባት ነገር አለ

## ግንቦት ሰባት versus ግንቦት ሀያ

### መልስ ፍለጋ ከብርሀኑ ጋር፤ ነጻ እንወጣ ዘንድ ምን እናድርግ?

እድን ዘንድ ምን ላድርግ እንዳለው መሆኑ ነው፡ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ። ከዚህ ቀደም የጻፍነውንን እየጻፍን እንዳልሆነ እንገምታለን። ቢሆንስ? ከዚህ ቀደም የጻፈውን ደግሞ የሚጽፍ እሱ "የሚናገረው ያለቀበት ነው" ብሎ የተናገረ ነቢይ፡ የደነገ ሀዋርያ፡ የቋጠረ አቃቤ-ነገር አለን? ብንደግመውም እውነት ነው። እውነትን ደግሞ እንናገራለን። ደግመን ደጋግመን እንመሰክራለን። እሱ ኢኮኖሚስት ነው። መምህርም ነው። ፖለቲከኛ ነው። እስረኛም ነው። ስደተኛም ነው። የሰብአዊ መብት ተከራካሪም። ቸርም ነው። ጓደኞቻችን ሲያወሩ እንደሰማነው፡ ደመወዙን እቤቱ ይዞ የማይገባ፡ ይልቅስ፡ ለነዳያንም ባይሆን ለወዳጆቹ የሚበትን ደግ። ሀሳቡን ከመናገር ወደኋላ የማይል ልበ ደንዳና፡ የሀሳብም የገንዘብም ደግ። ይሄ ባንድ ወገን ነው። ክፉንም ደግንም ሚዛን ላይ ማስቀመጥ መልካም ነውና፡ በሌላኛው ዘንድ ደግሞ ይሄንን እንደጀግና እንደአርበኛ ከሚቆጥሯቸው አለቆቻቸው ጋር አብሮ ቃሊቲ ወለል ላይ የከረመ እስረኛ "ባንዳ፡ ስልጣን ወዳድ፡ ክፉ ይሉታል"። እንደጠላት የፈረጅነውና እንደችግራችን ምንጭ አድርገን የቆጠርነው ኢህአዴግ ሳይሆን፡ እንደ ባልንጀራ የተሰልፍናቸው ግለሰቦችና ቡድኖች፡ ከጠላትም በላይ ጠላት ሆነው በተሰለፉበትና የሀገራችን ነገር ከምንም በላይ መፍትሄ አልባ በሆነበት ሰኣት ላይ ነው፡ የዛሬ ሶስት አመት የተነጠቅነውን ተስፋ፡ የተቀማነውን ድል ስናብሰለስል፡ ብርሀኑ፡ ብሬ፡ ወደ ከተማችን፡ ቫንኩቨርና ሲያትል የሚመጣው። ዛሬ የሀገራችን ጉዳይ "ከመቼውም በላይ"፤ "ከምንግዜውም በተለየ መልኩ፡" በከፋበት ሰዓት የሚሉትን ቃላት መጠቀም አይመቸንም። የሀገራችን ጉዳይ አምናም ካቻምናም፡ በሐይለስላሴም በደርግም ሰዓት፡ ሁሌም ከምንግዜውም በላይ እንደከፋ ነውና። ብቻ መለስ ብለን ስለብርሀኑ ስናስብ፡ ይሄ ይሄ ይታወሰናል። ወደዚህ ወደመንደራችን ከዘለቀ ደግሞ ይሄንን ቢያሰላስል ወደድን። እነሆ በትንሹ።

### በግንቦት ያጣነውን በግንቦት እናስመልስ

በዘጠና ሁለት ዓመታቸው ልጆቻቸው አነግ መሆናቸው በመጠረጠሩ ስምንት አመታት ሙሉ ያለፍትህ የታሰሩና የሚማቅቁ ዜጎችን ይዛ የምትሄድ ኢትዮጵያ አንፈልግም። ሳጥን ገልብጦና፡ ምርጫ አጭበርብሮ ለብቻው አራት ሚሊዮን ሚሊዮን ተመራጭ ወይም ለያንዳንዱ አምስት መራጭ አንድ ተመራጭ አሰልፌያለሁ ብሎ ሰውን በጥቅማጥቅም ለማሰር በሚጥርና በሚገዛ መንግስት መተዳደር አንሻም። ኢኮኖሚያችን እንዳደገ እየነገረን፡ ህዝቡን አመት በዓል በሽሮ በሚያሳድር መንግስት መገዛት አንገሽግሾናል። ዘፈናችሁ መረረኝ ብሎ በፈጠራ ክስ ወህኒ በሚከት ፍትህ ሚኒስቴር መተዳደር በቅቶናል። የራሷ እያረረባት የሰውን ታማስላለች እንዲሉ፡ የሰው አገር ድንበር ጥሶ ደም በሚያቃባ ስርአት መተዳደር መሮናል። መንገዱ ሁሉ በፌደራል ቅልብ በተሞላበትና ሰው ከቤቱ በወጣ ቁጥር፡ ዱላ ፈርቶ እንዲኖር ከተደረገበት ስርአት ስር መተዳደር በቅቶናል። ግን ደግሞ ስለበቃንና ስለመረረን ብቻ አልቀረልንም፡ አይቀርልንንም። በግንቦት ሰባት በቃን ስላልን አልበቃንም። ይሄንን የመከራ ዘመን የሚያሳልፍ :"ባህር የሚያሻግር ሙሴ" ያስፈልገናል። በዚያ ባርነት በከፋበት ዘመን ከፈርኦን አገዛዝ ነጻ የሚያወጣውን ስልት እንደቀየሰው ሙሴ፡ ከኢህአዴግ አገዛዝ ፈልቅቆ የሚያወጣ ንድፍ የሚነድፍ ነዳፊ፡ የትግላችን ቀያሽ ያስፈልገናል። ግን ደግሞ ፖለቲካ ብቻ የሚናገር አይደለም፡ ስንሰማውና ስንጋተው የከረምነውን የክስና የሽኩቻ ፖለቲካ ለውጦ፡ የመፍትሄ ሀሳብ ጠቁሞ መፍትሄው ላይ ነፍስ ዘርቶ፡ ሲጋና ደም አልብሶ የሚያሰልፍ ጀግናም ጭምር እንጂ። በዚህ ሰዓት ነው ብርሀኑ ወደ እዚህ ወደ ምእራብ ጫፍ የሚዘልቀው። ሲመጣም ይሄንን እንጠብቃለን። ብርሃኑ ሲመጣ ነገር ሁሉ ይለዋወጣል። ያኔም የሆነው እንደዚያ ነው። ግንቦት ሰባት።

### የጥያቄ መዓት የጥያቄ ናዳ

ጸሀይ በምስራቅ ወጣች። ንጉስ መወለዱን የምታበስር ኮከብም በምስራቅ ታየች። ምጽአትም በምስራቅ ነው ይባላል። እስኪ ዛሬ እንኳዋን ምእራቡ ይለፍለት። ዛሬስ ብርሀኑ በምእራብ ምን ይናገር ይሆን? በዲሲ ሰምተንሀል። በሎስ አንጀለስም አድምጠንሀል። በቺካጎም ተከታትለንሀል። እስካሁንም ግን መልስ ያልተሰጣቸው ብዙ አገራዊ ጥያቄዎች ሞልተዋል። ብርሀኑ የኢትዮጵያን ጥያቄዎችና መልሶች ሁሉ ተሸክሞ ይዞራል ብለን አናምንም። በመሰረቱ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያለው በኢትዮጵያዊያን ሁሉ እጅ ላይ እንጂ በግለሰቦች እጅ አይደለም። ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ አይነት ነገር ነው። ግን ደግሞ

እጆችን ሁሉ በእጅ ስራው የሚያስተባብር መፍትሄ ጠቋሚ ፈላስፋ ያስፈልገናል። ለዚህ ፍልስፍና የምናጨው ከብርሀኑ የተሻለ ፈላስፋ ማን አለ? ብርሀኑ ሆይ በግራ መጋባት ውስጥ የተቆለፈ፡ የሚያደርገው የጠፋው፡ የተጨነቀ ታዳሚ ነው የሚጠብቅህ። እንድን ዘንድ ምን እናድርግ እንልሀለን።

ወይስ ድነን ሳለ፡ ነገር ግን ዞር ብሎብን ይሆን እንዴ? አንዳንድ ሰዎች እንደሚያወሩት ኢትዮጵያ እያማረባት እኛ እየባሰብን እየፈለፈልን ይሆን እንዴ? ከገባንበት አጣብቂኝ እነደምን ልንወጣ ይቻለናል? አለም ከጎናችን ይሰለፍ ዘንድ ምን እናድርግ? ቀድሞውንስ ነገር እዚህ አሜሪካና አውሮፓ ተቀምጠን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ነጻ ማውጣት ይቻለናልን? ከዚህ ልናደረግ የምንችለው ተጨባጭ ነገር ምንድርነው? ሰላማዊ ትግል ምን ማለት ነው? ሰላማዊ ትግል ልክ አለውን? ድንበሩስ የት ድረስ ነው? ልክ በምርጫ 97 እንደታየው፡ የኢትዮጵያን ህዝብ ሁሉ የምናሳትፍበት የትግል ስልትና ድርጅት እንደምን ልንፈጥር ይቻለናል? እነዚህ ሰዎች አልተቻሉም፡ እውነቱን ለመናገር። ስለዚህ አፍንጫ አፍንጫቸውን በማለት ካልሆነ በስተቀር ልናወርዳቸው አንችልም የሚልና፡ የለም ከዚህስ በኋላ ቅንጣትም ደም መፍሰስ የለበትም የሚሉ ሀይሎች ባንድ ጠላት ላይ ተፋጠዋል። ይሄ መፋጠጥ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ግንቦት ሰባት ደረሰ። ግንቦት ሰባት።

**ብርሀኑ ሆይ፡ ስምህን ትሆን ዘንድ እንጠብቃለን**

ብርሀኑ፡ ዶ/ር፡ እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መመለስ አለበት ማለት አይደለም። ነገር በንግግሩ ሁሉ፡ እንዚህን መሰል ጥያቄዎች እንዳሉን ከግምት ሊያስገባና የስሙን ያህል ትንሽ ትንሽ ብርሀን ሊፈነጥቅባቸው ይገባል። በተረፈ እኛ እንደነዚያ እውቀት ማለት የቡርዡዋው ስርአት ያልሆነ ብቻ ነው ብለው መጽሀፍ እንዳቃጠሉ፡ (ስታሊን መሰል ቡድኖች ይላቸዋል፡ አንዱ ወዳጃችን) ግብዞች፡ መጽሀፍ የሚያቃጥል፡ ባንዳ ባንዳ የሚል ተሰላፊ ለንም። ያልገባንን እንጠይቃለን። ያጠራጠረንን እንመረምራል። መለስ ሊጠቁሙን ከሚችሉ ወይንም በመልስ ፍለጋ ሊያግዙን ከሚችሉ ጋር ተቀምጠን እንወያያለን። እነሆ ወደምእራብ አንጋጠን የሚመጣውን እንጠብቃለን።

ብርሀኑ፡ ወደዚህ ወደምእራብ ሰሜን አሜሪካ፡ እንኩዋን ደህና መጣህ።

እኛ የኢትዮጵያ ምእራባዊያን፡ ከምእራብ ሰሜን አሜሪካ፡